www. Ethiopiawinet.net

# የግንቦት ሰባት ተከሳሾች የሞት ቅጣት እንዲፈረድባቸው ተጠየቀ

(በታምሩ ጽጌ)

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ስርዓቱን በሀይልና በትጥቅ አመፅ ለመጣል፣ የጋራ የወንጀል አድማ ስምምነት በመፍጠር፤ የወንጀል ድርጊቱን አላማ፣ ውጤትና ፍሬሙሉ በሙሉ በመቀበል፣ በመደራጀት፣ በማደራጀትና በመምራት በሽብርና በአመፅ ተግባር ተሳትፈዋል ብሎ ጥፋተኛ የተባሉ 38 የግንቦት ተከሳሾችን በሞት እንዲቀጡ ፍርድ ቤቱን ጠየቀ፡፡ ዐቃቤ ሕግ በእነ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ መዝገብ ከተከሰሱት 11ኛ ተከሳሽ ሻለቃ አለማየሁና 17ኛ ተከሳሽ ሻለቃ አደፍርስ (ድርጊቱን ፈፅመናል ብለው ያመኑ ናቸው) በስተቀር በ38ቱ ተከሳሾች ላይ የሞት ቅጣት እንዲወሰንባቸው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎትን የጠየቀው፤ ሁሉም ተከሳሾች በተመሰረተባቸው አምስት ክሶች ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡፡

ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ የግል ነፃነታቸውን በተመለከተ፣ በባለቤትነት የተመዘገበ ንብረታቸው እንዲወረስ እና ከህዝባዊ መብታቸው ስለመሻር በሚል ሦስት ዓይነት የቅጣት ማክበጃዎችን አቅርቧል፡፡ አቶ መላኩ ተፈራ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ ሙሉነህ ኢዩኤል እና መስፍን አማን የቅንጅት ከፍተኛ የፖለቲካ መሪዎች ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ ሕዝብን በተሳሳተ መንገድ በመምራት፣ ብጥብጥና ሁከት በማነሳሳት ተከሰው በእድሜልክና (በአምስት ዓመት መላኩ ተፈራ) መቀጣታቸውን፤ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ከጠየቁ በኋላ ይቅርታ እንደተደረገላቸው ዐቃቤ ህግ ገልፆ፣ ተከሳሾቹ ካለፈው ስህተታቸው የማይታረሙ መሆናቸውን በዝርዝር በመግለፅ በወንጀለኛ ሕግ አንቀጽ 67"1"፣ 188"1) መሠረት ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰንባቸው ፍርድ ቤቱን ጠይቋል፡፡

ሁሉም ተከሳሾች የፈፀሙት ወንጀል ፍፃሜ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ፣ ሕገ መንግሥታዊ ስርዓቱን በማፍረስ ብቻ የሚቆም ሳይሆን በሕዝቦች እኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ በተመሠረተ አንድነት የተዋቀረውን ፌዴራላዊ ስርዓት የሚያፈርስ፣ የአገሪቱን አንድነት የሚበታትን፣ በአገር ህልውና ላይ ያነጣጠረ፣ የአንድ ወገንን ፍላጐት በሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ላይ የሚጭን፣ አገሪቱን ማብቂያ ወደ ሌለው ትርምስና የእርስ በርስ ጦርነት የሚከት አደገኛ አድራጐት መሆኑን የገለፀው ዐቃቤ ሕግ፣ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 258"ለ) መሠረት ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡
ሁሉም ተከሳሾች በተለያዩ ሀሳቦች፣ የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች እና የሙብት ጥሰቶች የተቋቋሙ ተደራራቢ አምስት ግዙፍ ወንጀሎች በመፈፀማቸው የሚጣለው ቅጣት በወ/ሕ አንቀፅ 85 እና 184 መሠረት ቅጣቱ መክበድ እንዳለበት መደንገጉንም አቃቤ ህግ ጠቅሷል፡፡

የወንጀሉ አፈፃፀምና ዘዴ ሲታይ አደገኛ የሽብር ተግባር ከመሆኑም በተጨማሪ በወንጀል ህግ አንቀፅ 84 (1""ሐ""መ) እና 183 መሠረት ከባዱ ቅጣት መወሰን እንዳለበት ዐቃቤ ሕግ

በቅጣት ማክበጃው ጠቅሶ፣ ከ11ኛና 17ኛ ተከሳሾች በስተቀር፣ በ38ቱ ተከሳሾች ላይ በወንጀለኛ ሕግ አንቀፅ 82 እና 179 መሠረት ሊነሱ የሚችሉ በማስረጃ የተደገፉ የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጠቅላላና ልዩ ማቅለያ እንደሌለ ገል"ል፡፡ በመሆኑም አጥፊዎቹ ሌላ ወንጀል እንዳይፈፅሙ ለመግታት፣ ለመሰሎቻቸው ቅድመ ማስጠንቀቂያና መቀጣጫ ለተቀረው ማስተማሪያ የሚሆን ጥፋተኛ በተሰኙበት አንቀፅ የተቀመጠው ቅጣት ጣሪያ (ከፍተኛውና የመጨረሻው) የሆነው የሞት ቅጣት እንዲወሰንባቸው ሲል ዐቃቤ ሕግ "የግል ነፃነታቸውን" በተመለከተ ባቀረበው የመጀመሪያ የቅጣት አይነት ስር ዘርዝሯል፡፡

የተከሳሾቹን ንብረት በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው የቅጣት ማክበጃ ሀሳብ ላይ እንደገለፀው፣ የወንጀለኛውን ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወረስ በሚል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 98/1/2/ መደንገጉን፣ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 99 መሠረት ደግሞ "ማንም ሰው በአገሪቱ ህገ መንግሥታዊ ስርዓት ወይም በውስጥና በውጭ ደህንነት ላይ አድማ በማድረጉ፣ ጉዳት የሚያደርስ ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት በሌለበት በሚፈረድበት ጊዜ ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት ጋር ንብረቱ እንዲያዝ ለማዘዝ እንደሚችል መደንገጉን ገል"ል፡፡

ዐቃቤ ሕግ ንብረትን በተመለከተ ጨምሮ የጠቀሳቸው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 260 መሠረት፣ 238፣ 240 እና 241፣ 246 እስከ 256 እና 252"2) መሠረት ፍርድ ቤቱ ከሚፈርደው ከዋናው ቅጣት ጋር አጣምሮ የተፈረደበት ሰው ንብረት በህጉ መሠረት እንዲወረስ ማድረግ እንደሚቻል መደንገጉን ዘርዝሯል፡፡

በተደነገገው ሕግ መሠረት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ ኮ/ል አለሁበል አማረ እና ያረጋል ይማም (ሚኪ) በሌሉበት ተከሰው ጥፋተኛ በመባላቸው በወንጀል ህጉ አንቀፅ 99 እና 260 መሠረት ንብረታቸው እንዲወረስ ዐቃቤ ሕግ ጠይቋል፡፡

ብ/ጄ/ ተፈራ ማሞ፣ አሳምነው ጽጌ፣ ጌቱ ወርቁ፣ ፅጌ ሃ/ማርያም በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ በመባላቸው በአንቀፅ 260 መሠረት ንብረታቸው እንዲወረስ በግልፅ በመደንገጉ፤ በስማቸው በባለቤትነት የያዟቸው የግል ንብረቶች እንዲወረስ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ፍርድ ቤቱን ጠይቋል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በመጨረሻም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 123 እና 124 መሠረት በፅኑ እስራትና ከዚያ በላይ ቅጣቶች የሕዝባዊ መብቶች መሻርን ሁኔታ የግድ ማስከተል እንዳለበት በመደንገጉ፤ ሁሉም ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት አንቀጾች መብት መሻርን የሚያስከትሉ በመሆናቸው የመብት መሻር ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጠይቋል፡፡

11ኛ ተከሳሽና 17ኛ ተከሳሽ ምንም እንኳን ከሌሎቹ ጋር የተጠቀሱት ድርጊቶችን ተጋሪ ቢሆኑም፤ ጥፋታቸውን ዘግይተው በማመናቸው መፀፀታቸውን ስለሚያሳይ ቅጣቱ ቢቀልላቸው ተገቢነው ብሎ ዐቃቤ ሕግ በማመኑ፣ በሞት ቅጣት ጥያቄው ውስጥ እነሱን አላካተታቸውም፡፡

ዐቃቤ ሕግ የቅጣት ማክበጃ ሀሳቡን ለፍርድ ቤቱ አቅርቦ ከጨረሰ በኋላ፣ ሁሉም ተከሳሾች በየተራ (እራሳቸው) የቅጣት ማቅለያ ሀሳባቸውን አቅርበዋል፡፡ ጥፋተኛ በተባሉበት ጉዳይ ህሊናቸውን የሚጎዳ፣ በሰውና በንብረት ላይ የደረሰ ምንም ዓይነት ጉዳት አለመኖሩን በመግለፅ የቅጣት ማቅለያ አስተያየታቸውን ያቀረቡት ብ/ጄ ተፈራ ማሞ ሲሆኑ፣ ከ18ት ዓመታቸው ጀምረው የደርግ አገዛዝን ለመጣል ከትጥቅ ትግሉ ጎን መሰለፋቸውን፣ በተለያዩ በአገሪቱ ክፍል በውጊያ ግንባር ተሰልፈው መዋጋታቸውና ማዋጋታቸውን፣ ከ28 በላይ ከፍተኛ ውጊያ ሲያደርጉ ሁለት እግራቸውን ተመትተው ግራ እግራቸው ሲያጥር በቀኝ እግራቸው ውስጥ ጥይት ገብቶ ለማውጣት በማይመች የሰውነታቸው ክፍል ውስጥ በመሆኑ በውስጣቸው እንደሚገኝ፣ ለ3 ጊዜ ከፍተኛ ተሸላሚ መሆናቸውን፣

የተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊነትና ወሳኝ ውጊያዎች ላይ መሳተፋቸውን፣ በተለይ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ከፍተኛ ግዳጅ መወጣታቸውንና መንግሥትም ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ 500 ካሬ ሜትር "ለቤተሰብህና ለራስህ" በማል እንደሸለማቸው ተናግረዋል፡፡

መንግሥት ከሸለማቸውና ትንሽ ሰርቪስ ቤት ሰርተውበት ከሚገኘው ቦታ ሌላ ምንም ነገር ወይም ንብረት እንደሌላቸው የገለፁት ብ/ጄ/ተፈራ፣ ለ26 ዓመታት አገራቸውንና ሕዝባቸውን ከማገልገል ውጭ አንድም ጊዜ ተከሰውም ይሁን ጥፋተኛ ተብለው እንደማያውቁ ተናግረዋል፡፡ አራት ልጆች እንዳሏቸውና በአጠቃላይ የ11 ቤተሰብ ኃላፊ መሆናቸውን የገለፁት ጄኔራሉ ፍርድ ቤቱ የነበራቸውን አገልግሎትና ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቅጣቱን እንዲያቀልላቸው ጠይቀዋል፡፡

ከሽግግሩ መንግሥት ቀደም ሲል ጀምሮ አቅማቸውና ችሎታቸው በሚፈቅደው መሠረት በአማራ ክልል በተለያዩ ሥራዎች፣ በባድመ ጦርነት የኮር አመራር በመሆን፣ በሐረር እና በተለያዩ ቦታዎች መንግሥትንና ሕዝብን ሲያገለግሉ መቆየታቸውን በመግለፅ የቅጣት አስተያየታቸውን ያቀረቡት አቶ አሳምነው ጽጌ ሲሆኑ፣ ወደ አሜሪካን አገር ተልከው ከፍተኛ ትምህርት ተከታትለው ከመጡበኋላ ለሦስት ዓመታት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች መንግሥትንና ሕዝብን ማገልገላቸውንና በአጠቃላይ ለ21 ዓመታት ያለምንም ጥፋት አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን ለፍርድ ቤቱ አስረድተዋል፡፡

የ4 ልጆች አባት መሆናቸውን፣ አባትና እናታቸውን እንደሚያስተዳድሩ አቶ አሳምነው ተናግረው፤ አዲስ አበባ ምንም ንብረት እንደሌላቸውና በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ክልል ሰበታ ላይ ብቻ በ200 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ ሁሉም ተከሳሾች በቅደም ተከተል የቅጣት ማቅለያ አስተያየታቸውን ሲያቀርቡ፣ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ከፍተኛ አገልግሎት ማበርከታቸውን፣ ሁሉም ከ15 ዓመታት በላይ ማገልገላቸውን፣ ምንም ዓይነት ወንጀል ፈፅመውና ተከሰውም እንደማያውቁ ተናግረው ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ተገንዝቦ ቅጣቱን እንዲያቀልላቸው ጠይቀዋል፡፡

ሻለቃ መኮንን ወርቁ፣ አቶ የሸዋስ መንገሻ፣ ወ/ሮ እማዋይሽ ወ/ሚካኤል "የፍርድ ቤቱን ውሳኔ እናከብራለን፤ ፍርዱን ለፍርድ ቤቱና ለእግዚአብሔር ትተናል" በማለት የቅጣት ማቅለያ አስተያየት አልሰጡም፡፡ 3ተኛ ተከሳሽ አቶ ጽጌ ሃ/ማርያም በተመለከተ በጠበቃቸው በኩል የቅጣት ማቅለያ አስተያየት የቀረበ ሲሆን፤ አቶ ፅጌ የ80 ዓመት አዛውንት በመሆናቸው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፅ 1ን የሚቃረን አንቀፅ በሳቸው ላይ መጠቀሱ አግባብ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ፍርድ ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

አቶ ጽጌ ከእንግሊዝ አገር ይዘውት በመጡት ወረቀት ምክንያት፣ ገንዘብ ለሰውሰጥተዋል በማልና በሌሎችም ምክንያት የተከሰሱ መሆናቸውን በመግለፅ የሞት ቅጣት አንቀፅ በሳቸው ላይ መጠቀሱ አግባብ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ውድቅ እንዲያደርገው ጠበቃቸው ጠይቀዋል፡፡ አቶ ጽጌ በሀይለሥላሴ፣ በደርግና በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ከፍተኛ ማህበራዊ ሥራ ሲሰሩ የነበሩ መሆናቸውን ጠበቃቸው አብራርተው፤ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ ከመነሻው ዝቅ ተደርጐ እንዲወሰንና በገደብ እንዲደረግላቸው ፍርድ ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

ንብረታቸውን በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ እንዲወርስ ማለቱን በመቃወም፣ ቤታቸው የብቻቸው ሳይሆን፣ ከሁለተኛ ባለቤታቸው የወለዱት ልጃቸው ጋር በጋራ የሚኖሩበት መሆኑንና የግላቸው ብቻ አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ እንዲጣራ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው የአቶ ጽጌ

ሃ/ማርያም ጠበቃ ጠይቀዋል፡፡

ዐቃቤ ሕግ ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል እንዲወርሱ የጠየቀውን የተከሳሾች ንብረት አጣርቶ እንዲያቀርብ፤ በቀረቡት ንብረቶች ላይ የጋራ ነው፣ ይመለከተኛል፣ ዕግድ አለበት የሚል ማንኛውም አካል ለህዳር 22 ቀን 2002 ዓ.ም. ይዞ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡